## ስለ ሊድ ምርመራ የሚከተሉት ነገሮች የሚመለከትዎ ከሆነ ሓኪምዎን ያነጋግሩ...

- ከውጭ የገቡ ቅመሞች እና አዩርቨዲክ የህንድ ባህላዊ የእምነት መድሃኒቶችን የሚጠቀሙ ከሆነ
- በቅርቡ ከውጭ ሀገር ወደ አሜሪካ የገቡ ከሆነ
- ወይም እርስዎ የሚያውቁት ሰው ሊድ ያለበት ቦታ የሚሰራ ከሆነ
- ከ 1978 በፊት የተሰራ ቤት አሳድሰው ከሆነ፤ ከአሸዋ ግርፍ ወይም ከተላላጠ ቀለም የተሰራ ቤት
- የሚጠጡት ውሃ ሊድ የያዘ መሆኑን የሚያውቁ ከሆነ
- አፈር፣ ጠመኔ፣ የሴራሚክ ውጤቶች፣ ፕላስተር፣ ወይም የቀለም ልጣጮችን ለመብላት ወይም የመብላት አባዜ ካልዎት
- ኢላማ መምታት፣ የአሣ ማጥመጃዎችን ወይም ጥይቶችን መበተን፣ ቀለም መቀባትን ወይም ሴራሚክ መስራትን የመሳሰሉ ለትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ የሚያደርጓቸው ነገሮች ለሊድ አጋላጭ ከሆኑ
- ከሊድ ማምረቻ ፋብሪካዎች፣ ማቅለጫዎች፣ የባተሪ ዳግመ ኡደት ድርጅቶች ወይም ሌሎች ሊድ የሚጠቀሙ ድርጅቶች አጠገብ የሚኖሩ ከሆነ
- የሊድ መጠን ታሪክዎ የሚያሳየው አምስት ማይክሮ ግራም በዴሲሌትር ወይም ኪዚህ በላይ ከሆነ

**ጥያቄዎች?**

**health.ny.gov/Lead**

NEW YORK STATE | Department of Health



# ነብሰጡር?

## አዲሱን ልጅዎ ከሊድ ብክለት ለመከላከል የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ምክሮች



## ማወቅ ያለብዎት:

ሊድ ነፍሰጡር ሴቶችን እና ጽንሳቸውን ሊጎዳ የሚችል ብረት ነው። አንጎልን፣ ኩላሊቶችን፣ ነርቮችን እና ሌሎች የሰውነት አካላትን ሊጎዳ ይችላል። ውርጃን፣ የመውለድ ውስብስብነትን እና ፅንስ የመያዝ ችግሮችን ሊፈጥር ይችላል። ሊድ በልጆች ባህሪ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ችሎታቸውን ያከብደዋል።

ሊድ በሴትየዋ ሰውነት ውስጥ ለዓመታት በመከማቸት፣ ከእናት ወደ ልጅ ሊያልፍ ይችላል።

ምንም እንኳን እንደ ንጥረ ነገር ሆኖ ባይካተትም፣ አንድ ምርት ሊድ ሊይዝ ይችላል።

አንዳንድ ነብሰጡር ሴቶች ምግብ ያልሆኑ ነገሮችን የመብላት አምሮት አላቸው። ይህ ባህርይ ደግሞ ፒካ ተብሎ ይጠራል።

## ምን ማድረግ ይችላሉ:

ነብሰጡር ከሆነ ወይም ለማርገዝ ዕቅድ ካደረጉ፣ የደም የሊድ መጠን ምርመራ ሐኪምዎን ይጠይቁ።

ከዚህ በፊት በተገኘው የምርመራ ውጤት በዴሲሌተር ከ አምስት ሚሊግራም በላይ የሆነ የሊድ መጠን ከተገኘብዎ፣ የወለዱት ልጅ ከሆስፒታል ከመውጣቱ በፊት የሊድ ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል።

ምግብ ያልሆኑ ነገሮች የመብላት ኣምሮትዎን ይቋቋሙ። የሚከተሉት ነገሮች ሊድ ሊይዙ ይችላሉ:


ጠመኔ


አፈር/ጭቃ/


የሴራሚክ ውጤቶች

## ከውጭ የሚገቡ ከመካከለኛው ምስራቅ ላቲን አሜሪካ, ደቡብ እስያ, እና ቻይና ሊድ ሊኖራቸው የሚችሉ ምርቶችን ያስወግዱ:


ቅመሞች፣ እርድን ጨምሮ።



ብዙ ዓይነት ከረሜላዎች።

የቆዳ ቅባቶች፣ እነዚህን ጨምሮ ኢሳውዳን ያውዳ፣ ሆንዳን እና ታናካ።



ኮስመቲኮች እንደ ኮህል(በሌላ አጠራር ሱማር ወይም ካሃል)።




በሊድ የተቀቡ ሴራሚኮች። አይጠቀሙ ለምግብ ማዘጋጃ እና ምግብ ለማቅረብ።


የኮስቲዩም ጌጣጌጦች፣ ብር ወይም ወርቅ የተቀቡትን ጨምሮ።

የዕጽዋት እና የአዩርቬዲክ መድኃኒቶች።




New York City Department of Health (የኒው ዮርክ ከተማ የጤና ዲፓርትመንት) ምስሎችን ይምረጡ